# በደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ የቀብር ስርዐት ሰበብ ከስዊድን የሚጻፈው ይብቃ!

የደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስን (የገሞራውን) የሥነ-ጽሁፍ ሥራ ታላቅነት ከሚያደንቁትና ከሚያከብሩት በርካታ ኢትዮጵያዊያን መሀል አንዱ ከመሆኔ በተጨማሪም ትህትናውን፣ ቸርነትና ደግነቱን፣ ሰው አክባሪና አፍቃሪነቱን በቅርብ የመመስከር እድል ካገኙት ብዙ ወዳጆቹ መሃልም እቆጠራለሁ ብየ ለመናገር እደፍራለሁ። ስለሥራው ታልቅነትም ሆነ፣ ስለሰባዊ ማንነቱ እንዲሁም በስደት ኑሮ ስለደረሰበት መንገላታት በቂ ትኩረት ተሰጥቶት በትክክለኛ መረጃና ጥናት ላይ የተመሠረተና በአስተማማኝ ባለሙያዎች የተጻፈ ሰነድ ወደፊት ለታሪክ ይቀርባል የሚል ምኞትና ተስፋ አለኝ።

ይህንን አጭር ጽሑፍ እንዳቀርብ የተገደድሁት ግን ታሪክን የሚያዛባ፣ አንባቢንና ሰሚን ግራ የሚያጋቡ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች በተለያዩ ድህረ-ገጾች ከስዊድን በተደጋጋሚ በመሰራጨቱ ነው። እነዚህ ጽሁፎች በደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ የቀብር ሥርዐት ላይ የተመርኮዙ ናቸው። በቅርብ የማውቀው ጉዳይ ተጣሞ በጽሁፍ ሲቀርብ ዝም ማለቱ ትክክል መስሎ ስላልተሰማኝ ውነቱን በዚህ ጽሁፍ ለማያውቁ ለማሳወቅ አቀርባለሁ። አላማዬም ይህ ብቻ ነው።

## 1. የደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ በሞት መለየት፣ ዜናውና የቀብሩ ውሳኔ

ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ በሕይወት እያለ፤ በጤና ጉድለት የተነሳ የኅብረተሰቡ ርዳታ ባስፈለገው ጊዜ ከህክምና ሰጭዎችና ከመሳሰሉት መንግሥታዊ መአከሎች ጋር ላለው ግንኙነት የቅርብ ተጠሪ አቶ ዘነበ በቀለ ነበር። በዚህም ሚናው የተነሳ የገሞራው ማረፍ በ**ኖቬምበር 10**፣ ዕለተ ሰኞ ተደውሎ የተነገረው ለእሱ ነበር። ወዲያውኑ የቅርብ ወዳጆች ተጠራርተን አቶ ዘነበ ቤት በዚሁ ዕለት ተገናኝተን ከሰአት በኋላ ጉዳዩን ወደያዘው መሥሪያ ቤት ተያይዘን ሄድን። አቶ ዘነበም ጉዳዩን ከያዘው ሰው ጋር ተነጋግሮ ያገኘው መረጃ የእሱ ተጠሪነት ከአቶ ኃይሉ ሞት ጋር ያበቃ በመሆኑ፤ ቀብሩን ለማዘጋጀት የአቶ ኃይሉን ዘመዶች ውክልና ማምጣት እንዳለበት ነበር።

በዚሁ መሠረት የሟቹ የአንደኛው ወንድም ልጅ ለአቶ ዘነበ በቀለ በአስቸኳይ የውክልና ወረቀት ስትልክ በዚያው ሳምንት ደግሞ የሌላ ወንዱሙ ልጆች አቶ አብነት እሸቱን መወከላቸው ተሰማ፡ የአቶ ዘነበ በቀለ ወካይ የአቶ ኃይሉ አስከሬን አገሩ ሄዶ ከወላጆቹና ከወንድሞቹ ጎን እንዲያርፍ እንደምትፈልግ ውሳኔዋን ስትናገር፣ የአቶ አብነት ወካዮች ደግሞ ስዊድን እንዲቀበር ይፈልጋሉ ሲል አቶ አብነት ራሱ ተናገረ። ለስቶክሆልም ነዋሪዎች የተሰማው የሚቹ የወንድም ልጆች ስዊድን ወይም ኢትዮጵያ ይቀበር በሚለው ውሳኔ ላይ አልተስማሙም የሚል ነበር። እውነቱን የሚያውቁት ግን ወካዮችና ተወካዮች ናቸው።

አርብ **ኖቬምበር 14** ቀን ከአቶ ዘነበ፣ ከአቶ አብነትና ከሌሎች ሁለት ጓደኞቼ ጋር ሆነን በቀብሩ ጉዳይ ተገናኝተን ስንነጋገር፤ አቶ ዘነበና አቶ አብነት አቶ ኃይሉ ስዊድን መቀበር አለበት የሚል አቋም ሲይዙ፤ ምንም እንኳን እኔ ተወካይ ባልሆንም፤ የኔ ሃሳብ "እንደግለሰብ ፍላጎቴን ከተጠየቅሁ የትውልድ አገሩ ሄዶ ከወላጆቹና ከወንድሞቹ ጎን ቢያርፍ እመርጣለሁ፣ ግን ውሳኔው የዘመዶቹ ስለሆነ እዚያም ይሁን እዚህ ለአቶ ኃይሉ ተብሎ በሚደረግ ማንኛውም ነገር እተባበራለሁ" የሚል ነበር።

በሳምንቱ ሰኞ **ኖቬምበር 17** ቀን አቶ ዘነበን፣ የአቶ ኃይሉን ጉዳይ የያዘው ፖሊስ ቀጥሮት ስለነበር ፖሊሱ የሚለውን ከሰማን በኋላ ቀብሩን እንድናዘጋጅ ተገናኘን። አቶ ዘነበና አቶ አብነት ስዊድን መቀበር አለበት የሚል አቋማቸውን አልቀየሩም። የአቶ ዘነበ ወካይ ኢትዮጵያ መቀበር አለበት ብላለች፣ የአቶ አብነት ወካዮች ደግሞ ስዊድን ብለዋል ተባለ። ከዚህም ተጨማሪ፤ አቶ አብነት "ፖሊስ የቀጠረኝ ለአርብ **ኖቬምበር 22** ቀን ስለሆነ እስከዚያ ምንም መሥራት ስለማንችል አርብ **ኖቬምበር 22** ቀን እንገናኝ" አለ። እኔም በተባለው ቀን የመገናኘት ፍላጎት እንደሌለኝና እንደማልገኝም ገለጽሁ። ስለዚህም በተባለው አርብ ኖቬምበር 22 ቀን አልተገኘሁም።

በኋላ ግን የሁለቱ ወንድማማች ልጆች ተስማምተው ለአቶ ዘነበ በቀለና ለአቶ አብነት እሸቱ የሰጡትን ውክልና አንስተው **በኖቬምበር 22** አርብ ማታ ሌላ ሰው በጋራ የወከሉበትን ሰነድ ላኩ፣እንዲሁም የሁለቱ ወንድማማች ልጆች የአቶ ኃይሉ ገብረዮሐንስ አስከሬን ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ከወንድሞቹና ከወላጆቹ ጎን በቤተሰብ መቃብር እንዲያርፍ መወሰናቸውን ጨምረው አሳወቁ።

## 2. የቀብሩ ተግባር አፈጻጸም

በቤተሰብ በጋራ የተወከለው ግለሰብም ቅዳሜ **ኖቬምበር 23** ለሟቹ አክብሮትና ፍቅር አላቸው የሚላቸውን 4 ሰዎች ጠርቶ እንደ ሟቹ ቤተሰቦች ፍላጎት የቀብሩንና የሽኙቱን ስነ-ሥርአት ለማዘጋጀት እንዲረዱት ከጠየቃቸው አንዱ እኔ

ነበርሁ። እኔም ጥሪውን በደስታ ተቀበልሁ። ከተሰበሰብነው አምስት ሰዎች መካከል ከኔ በቀር ከላይ በጠቀስኳቸው ሂደቶች ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበራቸውና ጥሪውን ብቻ አክብረው የተገኙ ናቸው። ሥነ-ስርዐቱን የመምራት፣ የሥርዐቱን ይዘት የሚገልጽ ወረቅት የማተም፣ ለዕለቱ ተገቢ የሆኑ የተለያዩ ጽሁፎችን የማቅረብና ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸውን ሌሎች ግለሰቦች የማነጋገር ኃላፊነት ተከፋፍለን ተለያየን። አቶ ዘነበ በቀለ በስልክ ሊገኝ ባላመቻሉ እሱን ፈልጎ ማገኘቱም አንዱና ቀዳሚው ተግባር መሆኑ ታምኖበት የሥራ ክፍፍሉ ውስጥ ገብቶ ነበር፤ ግን ለማግኘት የተደረገው ጥረት ፍሬ ሳይሰጥ ቀርቷል።

የአቶ ኃይሉ ማረፍ ከታወቀ **ከኖቬምበር 10** እስከ **ኖቬምበር 24** ድረስ የአቶ ኃይሉ ቤተሰቦች የጋራ ውሳኔና የፖሊሱ መልስ ይጠበቅ ስለነበር፤ ለቀብር ዝግጅት የተሠራ አንድም ነገር አልነበረም። ስለዚህ ከሰኞ እስከ አርብ በነበሩት 5 ቀኖች ውስጥ ጉዳዮችን ጨርሶ እሁድ ቀብሩን አዲስ አበባ ለማስፈጸም መነሳት ቀላል ተግባር አልነበረም። የአቶ ኃይሉን መሞት የሚያረጋግጥ ወረቀት (ዴዝ ሰርቲፊኬት) ከሀኪም ማውጣት፣ ለአስከሬኑ ተገቢው እንክብካቤ መደረጉን ማረጋገጥ፣ ቀባሪ ድርጅት ማነጋገር፣ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሀዘንተኞችን የሚያስተናግድ የቤተክርስቲያን አዳራሽ ፈልጎ መከራየት፣ ከሥርአቱ በኋላ ሀዘንተኞቹ የሚስተናገዱበት አዳራሽ መከራየት፣ ጸበል ጻዲቅ ለመጋበዝ ፍላጎታቸውን የገለጡ ወገኖችን ማስተባበር፣ከስዊድን የመልቀቂያ ሰንዶችን ከተለያዩ የመንግሥት ተቋሞች ማውጣት፣ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሟቹን ማንነት ማስመስከር፣ ወደኢትዮጵያ የመግቢያ ቪዛ ማሠራትና ትራንስፖርት ማዘጋጀት ከብዙዎቹ በከፊሉ የሚጠቀሱ ዋና፣ ዋና ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ተግባራት በብዛት በተወካዩ ትከሻ ላይ ያረፉ ነበሩ። ይህ ሰው ግን ሠርቶ ማሠራት የሚችል የተፈጥሮና የእውቀት ልዩ የመምራት ችሎታ ያለው ትልቅ ሰው ነው። ለዚህ ሰው ያለኝ አክብሮትና አድናቆት የላቀ መሆኑን ከልብ እገልጻለሁ።

### 3. የሽኘት ሥነ-ስርዐት በስቶክሆልም ከተማ

በመጨረሻም ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ/ገሞራው በብዙ መቶ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሀዘንተኞች በተሳተፉበት ሥነ-ስርዐት እ.ኤ.አ. ቅዳሜ **ኖቬምበር 29** ቀን 2014፣ በስቶክሆልም ከተማ ሽኝት ተደርጎለታል። ከስዊድን ኗሪዎች በተጨማሪ፣ ከጀርመን፣ ከሆላንድ፣ ከኖርዌይና ከሌሎችም አገሮች የመጡ ኢትዮጵያዊያን የስርዐቱ ተሳታፊዎች ነበሩ።

የስቶክሆልም መድህኔአለም ቤተክርስቲያን በብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ኤልያስ፤ የአውሮፓና የምስራቅ አፍሪካ ሊቃነ ጳጳስ፤ የሚመራ ፍትሀት አካሂዳለች። ከዚያም በመቀጠል የተለያዩ ግጥሞች ተነበዋል፣ ስለሕይወት ታሪኩና ስለአኗኗሩም አጫጭር መግለጫዎች ተሰጥቷል። በመጨረሻም የቤተክርስቲያኑ አዳራሽ ጠብቦት ውጭ የቆመው ሀዘንተኛ ሁሉ አስከሬኑን ተሰናብቶ ጸበል ጻዲቅ ወደ ተዘጋጀበት ቦታ በመጓዝ የጋራ ሀዘኑን በአንድ ላይ የማስተናገድ ተጨማሪ ዕድል ማግኘት ችሏል። ይሄንንም የሚያስደንቅ ዝግጅት ባጭር ጊዜ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ያቀረቡ የአቶ ኃይሉ ወዳጆች፣ አድናቂዎችና አክባሪዎች እህት ወንድሞቻችን ከፍተኛ ምስጋና ይድረሳቸው።

ከስርዐቱ በኋላ አስከሬኑ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ለደህንነት ሲባል አስከሬኑ 24 ሰዓት አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ መቆየት አለበት ተባለ።ይህ ዜና ቀደም ብሎ ያልታሰበና የማይታወቅ ነበር።

### 4. የቀብር ስርዐት በአዲስ አበባ

**ኖቬምበር 30** አስከሬኑ ከስቶክሆልም ከተማ ተጉዞ ሰኞ **ዲሴምበር 1** ቀን ቦሌ ሲደርስ ብዙኃን ሀዘንተኞች እንደተቀበሉት ማወቅ ተችሏል። ከዚያም ታጅቦ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ደርሶ 1ኛ- ቤተዘመዶች፣ 2ኛ- የደብረ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ቄሳውስት 3ኛ- የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፣ 4ኛ- ጓደኞችና አድናቂዎች በተገኙበት ከፍ ባለ ሥነ-ስርዐት ስርዐተ-ፍትሀት ተደርጎለት ከወላጆቹና ከወንድሞቹ ጎን አርፏል።

***መደምደሚያና ቅሬታ***

በቁጥር 1. እንደገለጽሁት የአቶ ኃይሉ ገብረዮሐንስን የቀብር ቦታ መወሰን የሚችለው ቤተሰብ ብቻ መሆኑን የወሰነው የስዊድን ፖሊስ ነው፤ ውሳኔውም በአገሩ ሕግ ላይ የተመሠረተ ነው። ለአቶ ዘነበ በቀለና ለአቶ አብነት እሸቱ ውክልና የሰጧቸውም ሆነ በኋላ ውክልናዉን የቀየሩት ህጋዊ የሆኑ የሟቹ ቤተሰቦች ናቸው። የስዊዲንን ሕግ ለመደንገግም ሆነ የቤተሰብን ፈቃድ ለማስለወጥ፤ መጨረሻ ላይ ውክልና የተሰጠው ሰውም ይሁን ሥነ-ስርዐቱ በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄድ የተሰጣቸውን ድርሻ ያበረከቱት ግለሰቦች የተጫወቱት ምንም አይነት ሚና የለም። ተሳትፏቸው የተመሠረተው ለደራሲውና ለሰው አፍቃሪው ለአቶ ኃይሉ ገብረዮሐንስ ባላቸው አክብሮትና አድናቆት ላይና በባህልና በእድገት በወረሱት የኢትዮጵያዊነት አደራና ግዴታ ነው።

ነገር ግን አቶ ዘነበ በቀለና ሌላ ስሙን ለመግለጽ ድፍረት የሌለው ግለስብ የአቶ ኃይሉን ኢትዮጵያ መቀበር አጥብቀው መቃወማቸውን እየገለጹ ለሰሚ ግራ በሚያጋባ መንገድ፤ ሌላው ቀርቶ በጉዳዩ ጨርሶ የሌሉበትን ግለሰቦች ሳይቀር በክህደትና ለስማቸው አስነዋሪ ቅጽሎችን በመጨመር በተደጋጋሚ በደብተራውና በኢኢድን እንዲሁም በኢትዮፓትሪዮት ድህረገጾች ላይ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች አውጥተዋል። በእነዚህ ጽሁፎች ውስጥ ስማቸው አስነዋሪ ቅጽል ተጨምሮበት የሚነሱት ግለሰቦች ከፊሎቹ በመሸኛው ስራ ውስጥ በምንም አይነት መልኩ ያልተሳተፉ ሲሆኑ፤ የተሳተፉት ደግሞ እዚህ ጽሁፍ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ምንም አይነት ሚና ያልተጫወቱ ናቸው። ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ከመነሳቴ በፊት ከተጠቀሱት ግለሰቦች ከብዙዎቹ ጋር ተነጋግሬአለሁ። በድህረገጾቹ ላይ የወጡትን ጽሁፍችም ከሞላ ጎደል አንብቤ ኮፒ አድርጌም አስቀምጫለሁ። እንዲሁም የግለሰቦችን ምንነትና ማንነት በሚዳፈር መልክ ስም እየጠሩ መጻፍ በምንም መልኩ መልካም ነው ሊባል አይቻልም።ኢትዮጵያዊ ጨዋነትንም ሆነ ትክክለኛነት አለው ለማለት አያስደፍርም ብዬ አምናለሁ።

የዚያ ታላቅ ባለሙያ የአቶ ኃይሉ ገብረዮሐንስ/ገሞራው ስም መነሳት ያለበት በሥራውና በትልቅ ባህሪው እንጅ፤ ትክክለኛነት በጎደለው መልኩ መሆኑ እኔን እንዳሳዘነኝ ብዙዎችን ቅር ሳያሰኝና ሳያሳዝን አይቀርም። እኔ እስከማውቀውም ድረስ እዚህ ጽሁፍ ላይ ከሰፈረው ውጭ የተፈጸመ ሌላ ተግባር ስለሌለ፤ የትልቁን የአቶ ኃይሉ ገብረዮሐንስ/የገሞራውን አስከሬን በክብር እንዲያርፍ ትብብር ላደረጉት ግለሰቦች ሁሉ ትልቅ አክብሮት እንዳለኝ እገልጻለሁ።




ስዩም ሐዲስ

ስቶክሆልም ዲሴምበር 2014.